

የአንደኛ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጣዊ ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ

የካቲት 2017 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

መግቢያ

ሀገራት የነደፏቸውን የልማት እቅዶችን ለመተግበር በሁሉም ደረጃ የሚያስፈልገውን የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ ከሚተገበሩ ስትራቴጂዎች ጎን ለጎን በየደረጃው የትምህርት ጥራቱን ለማስጠበቅ በርካታ ተግባራት የሚያከናውኑ ሲሆን ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ማድረግ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያገኘ መሠረታዊ መብት ነው። ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት በትምህርት ቤቶች የሚካሄድ ተከታታይነት ያለው የውስጥና የውጪ ኢንስፔክሽን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻልና የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

የትምህርት ሚኒስቴር አጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የግምገማ ውጤት ለትምህርት ቤቶች ማሻሻያ መርሀ ግብር ተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ መረጃ የሚሰጥበት ሂደትና በየደረጃው ድራፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ነው። የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የስራ ክፍል በ2004 ዓ.ም በማቋቋም በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ በነበረው የትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን መመሪያና ማዕቀፍ ለትምህርት ቤቶች እየተሰጠ ያለው የኢንስፔክሽን አገልግሎት ወጥነት ባለው መልኩ ሲተገበር ቆይቷል። ይሁን እንጂ ማዕቀፉ ከትምህርት ቤት ማሻሻል ማዕቀፍና የት/ቤቶች ስታንዳርድ ጋር የተናበበና የተገናዘበ ለማድረግና በተለይም ለትምህርት ቤቶች በሚሰጠው የኢንስፔክሽን አገልግሎት ድጋፋዊ ኢንስፔክሽን መልክ እንዲይዝ ለማድረግ እስካሁን የጋጠሙ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ሊሰጥ በሚችል መንገድ አሻሽሎ ለማዘጋጀት ተሞክሯል። በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽለው የተዘጋጁትን የትምህርት ቤቶች ስታንዳርዶችን መሰረት በማድረግ እንዲዘጋጅ በመወሰኑ የመጀመሪያ፣ የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። ማዕቀፉ የኢንስፔክሽን አላማዎች፣ መለኪያዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ ስታንዳርዶች አመልካቾችንና ገላጮችን ይዟል።

2. የኢንስፔክሽን አላማዎች

2.1. አጠቃላይ ዓላማ

የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር፣ በውጤታማነት ማደጉን፣ የመማር ማስተማር ስራ ውጤታማ መሆኑን፣ ምቹ የመማሪያ እና የትምህርት ቤት አካባቢ መፈጠሩን፣ የወላጅ እና የህብረተሰብ ግንኙነትና አጋርነት መጠናከሩን በመመዘን ድጋፋዊ ኢንስፔክሽን ምዘና ማከናወን ነው።

2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የትምህርት ቤቱ አመራር ብቃት ያለው አመራር በመስጠት፣ ግለ-ግምገማ በማካሄድ፣ የቅድሚያ የትኩረት ጉዳዮችን በመለየት ጥራት ያለው ስትራቴጂካዊ እና ዓመታዊ እቅድ በማዘጋጀት፣ ተግባሪዊ በማድረግ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ መሻሻሉን ማረጋገጥ፣
- የመምህራንን የማስተማር ውጤታማነት በማሳደግ የተማሪዎችን ውጤት እና ስነምግባር መሻሻሉን ማረጋገጥ፤
- ተገቢውን ግብዓቶች በማሟላት እና የአሰራር ስርአቶችን በመዘርጋት ለሁሉም ተማሪዎች፣ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ተስማሚ እና አመቺ የትምህርት ቤት አካባቢ መፈጠሩን ማረጋገጥ፤
- በትምህርት ቤት፣ በወላጅ እና በህብረተሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ማረጋገጥ፤

3. የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን መለኪያዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ ስታንዳርዶች እና አመልካቾች፡፡

3.1. ግብዓት (Input) የተሰጠ ክብደት 20%

3.1.1. ምቹ እና ሰላማዊ የመማሪያ አካባቢ

3.1.1.1. ፋሲሊቲ እና መሰረተ ልማት /8%/

ስታንዳርድ 1 .በትምህርት ቤቱ በስታንዳርድ መሰረት የቦታ ስፋት፣ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች እና ቦታዎችን መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡ /5%/

አመላካቾች፡-

1.1. ትምህርት ቤቱ ተፈላጊውን የቦታ ስፋትና የይዞታ ማረጋገጫ ስለማሟላቱ፤ /0.5%/

1.2. ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት (ቤተ-መፅሃፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ) መሰረተ ልማቶች በስታንዳርዱ መሰረት የታነፁ ስለመሆናቸው፣ /1%/

1.3. በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባራት የሚካሄድባቸው መሰረተ ልማቶች (መማሪያ ክፍሎች፣ የመምህራን ማረፊያና አስተዳደር ቢሮዎች፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወዘተ...) በስታንዳርዱ መሰረት የታነፁ ስለመሆናቸው፣ /1%/

1.4. በትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ ጋር ስለመሟላቱ፤ /0.5%/

1.5. ትምህርት ቤቱ በቂ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት ስለመኖሩ፤/0.5%/

1.6. ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል መሰረተ ልማቶች (ለእርሻና ለእርባታ ቦታዎች፣ ለእድ ጥበብ መስሪያ) በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የታነፁ ስለመሆናቸው፤ /1%/

1.7. ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የስራና ተግባር ትምህርቶች ሰርቶ ማሳያነት /Works hop/ የሚያገለግሉ ክፍሎች አሟልቷል፡፡ /0.5%/

ስታንዳርድ 2. ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለመማሪያ፣ ለአገልግሎት መስጫ ክፍሎች እና ቦታዎች የሚያገለግሉ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን /ግብዓቶችን/ መሟላታቸው ተረጋግጧል፡፡ /3%/

አመላካቾች፡-

2.1. ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት (ቤተ-መፅሃፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ) በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቁሳቁሶችን ስለመሟላቱ፣ /0.5%/

2.2. ት/ቤቱ የመማሪያ፣ የቤተ-ሙከራዎች፣ የመምህራን ማረፊያ፣ መመገቢያ አዳራሽ እና አስተዳደር ክፍሎችን ከአስፈላጊ ቁሳቁሶች ጋር ስለማማላቱ፣ /1%/

2.3. ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል (የእርሻና የእርባታ ቦታዎች፣ የእድ ጥበብ ሰርቶ ማሳያዎች የእንጨትና ብረታ ብረት ስራ ቦታዎችን ወዘተ) ቁሳቁሶችን /ግብዓቶችን/ ስለመሟላቱ፡፡ /1%/

2.4. ትምህርት ቤቱ ተግባራዊ እያደረገ ለሚገኝባቸው ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የስራና ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ (ለማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ፣ ለህንፃ ግንባታ ቴክኖሎጂ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ለግብርና ሳይንስ፣ ለጤና ሳይንስ፣ ለተግባቦትና ማህበራዊ ሳይንስ፣ ለቢዝነስ ሳይንስ፣ ለክዋኔና ለትዕይንት ማቅረቢያ ወዘተ) የማሰልጠኛ አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች ጋር ስለመሟላቱ፣ /0.5%/

3.1.2. ምቹ አካባቢ /4%/

ስታንዳርድ 3. የትምህርት ቤቱ ውስጥና ውጫዊ አካባቢ ምቹና ደህንነቱ የማያሰጋ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /2%/

አመላካቾች፡-

3.1. በት/ቤቱ የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለሁሉም ተማሪዎች ምቹ ስለመሆናቸው፤ /1%/

3.2. የትምህርት ቤቱ አካባቢ ከአዋኪ ጉዳዮች የጸዳ ስለመሆኑ፤ /1%/

ስታንዳርድ 4. ት/ቤቱ ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው እና ለሴት ተማሪዎች ምቹ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /2/

4.1. ትምህርት ቤቱ ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ፤ /1/

4.2. ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ፡ /1/

3.1.3. ፋይናንስና የሰው ሃይል /8%/

ስታንዳርድ 5. ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ተግባራት የፋይናንስ ሀብት አሰባስቧል፤ /3/

አመላካቾች፡-

5.1. ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ ሀብት የሚያሰባስብበት እቅድ ስለማዘጋጀቱ፤ /1%/

5.2. በእቅዱ መሰረት ሀብት ስለማሰባሰቡ፣ /1/

5.3. በእቅዱ መሰረት ፕሮጀክት በመቅረፅ ሀብት ስለማሰባሰቡ፣ /0.5/

5.4. በወረዳው / ከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊውን በጀት ስለመመደቡ፤ /0.5/

ስታንዳርድ 6. በትምህርት ቤቱ የትምህርት ቤት አመራር፣ መምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ተሟልቷል፡፡ /4%/

አመላካቾች፡-

6.1. **ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ስለማሟላቱ፤ /1%/**

6.2. **ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው የትምህርት ቤት አመራሮች ስለማሟላቱ፤ /1%/**

6.3. **ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የአስተዳደር ሰራተኞችን ስለማሟላቱ፤ /1%/**

6.1. **ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው መሰረት ተማሪዎችን የመደልደል ስራ አከናውኗል ፤ /1%/**

ስታንዳርድ 7. አመራሩ አሳታፊ የትምህርት ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ /1/

አመልካች፡-

7.1. **አመራሩ የትምህርት ቤት ግለ ግምገማ እንዲካሄድ ስለማድረጉ፣ /0.5%/**

7.2. **የሦስት ዓመት ስትራቴጂክ እና አመታዊ የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ከግለ ግምገማና ኢንስፔክሽን ግብረ-መልስ በመነሳት ባለድርሻ አካላትን አሳትፎ ስለማዘጋጀቱ፤ /0.5/**

3.2. ሒደት (60%)

3.2.1. የትምህርትቤት አመራርና አስተዳደር /35%/

3.2.1.1. የመምራት ብቃት /10%/

አመልካች፡-

ስታንዳርድ 8. አመራሩ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋት፣ የለውጥ እና የህዝብ ግንኙነት ሥራን በአግባቡ የመምራት ክህሎት አድጓል፤/4%/

8.1. **ከትምህርት ቤት መሻሻል ጋር ተያይዘው የሚመጡ የለውጥ ስራዎችን በአግባቡ ስለመምራቱ፤ /1%/**

8.2. አመራሩ በትምህርት ቤቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በወቅቱ የማስተዋወቅ ተግባር ስለማከናወኑ፤ /1%/

8.3. የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ ያሉ እና ከሌሎች የተገኙ መልካም ልምዶችን፣ ዕውቀቶችንና ተሞክሮዎችን ቀምሮ ተግባራዊ ስለማድረጉ፣ /1% /

8.4. አመራሩ እና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ስለመፍጠሩ፤ /1%/

ስታንዳርድ 9. የትምህርት ቤቱ የአመራር የራሱን፣ የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኛውን ሙያዊ ክህሎት ለማዳበር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስልጠና አዘጋጅቶ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ /3/

አመልካች፡-

9.1. አመራሩ የራሱንና የመምህራን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል የአቅም ግንባታ መርሃ ግብር አውጥቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ፣ /1%/

9.2. የአስተዳደር ሰራተኞችን ሙያዊ ክህሎት የማሻሻያ ተግባራት ስለማከናወኑ፣ /1%/

9.3. የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ ስለማግኘቱ፣ /1%/

ስታንዳርድ 10. የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መተግበራቸውን አረጋግጧል፡፡ /3%/

አመልካች ፡-

10.1. የት/ቤቱ አመራር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን በማደራጀት ተግባርና ሃላፊነታቸውን ስለማውረዱ፤ /0.5/

10.2. የት/ቤቱ አመራር ለአደረጃጀቶች የሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነት አፈጻጸም በየወቅቱ ስለመደገፉ፤ ስለመከታተሉና ግብረ-መልስም ስለመስጠቱ፤ /1/

10.3. የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴን የእቅድ አፈፃፀሞች ስለመከታተሉ፤ ስለመደገፉና ግብረ-መልስ ስለመስጠቱ፤ /1%/

10.4. በትምህርት ቤቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት አመራሩ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያሳትፍ ስርዓት ስለመዘርጋቱ፤ /0.5%/

3.2.1.2. የማስተማር ሂደት እና ተነሳሽነት /8%/

ስታንዳርድ 11. በትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ተፈጥሯል፡፡ /4/

አመልካች ፡-

11.1. አመራሩ የውስጥ ሱፐርቪዥን ስርዓት በመዘርጋት ለመምህራን ሙያዊ ድጋፍ ስለመስጠቱ፤ /1%/

11.2. መምህራን እርስ በእርሳቸው የክፍል ውስጥ ምልከታ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ፤ /1%/

11.3. መምህራን ለተማሪዎች ተከታታይ ምዘና እና ግብረ-መልስ መስጠታቸውን ስለመደገፉና ስለመከታተሉ፤ /1%/

11.4. የመምህራን እና የተማሪዎችን የአመራር ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /1%/

ስታንዳርድበ 12. በትምህርትቤቱ አመራር የመምህራን የማስተማር ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት መፈጠሩ ተረጋግጧል፡፡ /4/

አመልካች ፡-

12.1. የት/ቤቱ አመራር ስኬታማ ግለሰቦችን በመጋበዝ ሙያዊ ተሞክሮዎችን እንዲያካፈሉ ስለማድረጉ፤ /1%/

12.2. በስታንዳርዱ መሰረት ለመምህራን ምቹ የስራ አካባቢ ስለመፈጠሩ፤ /1%/

12.3. የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው መምህራን የሚበረታቱበት ግልፅ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ፤ /1%/

12.4. የት/ቤቱ አመራር ሁሉም መምህራን በእኩልነት /በውሳኔ ሰጭነት/ የሚሳተፉበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣ /1%/

3.2.1.3. የት/ቤት አስተዳደር /5%/

ስታንዳርድ 13. የትምህርት ቤቱ አመራር መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞችን በአግባቡ በመመደብ ተግባርና ሀላፊነታቸውን መወጣታቸውን መከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፤ /3%/

አመልካች ፡-

13.1. ሁሉም መምህራን በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ ስለመደረጉ፤ /0./5%/

13.2. ሁሉም የአስተዳደር ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ ስለመደረጉ፤ /0.5%/

13.3. የትምህርት ቤቱ አመራር መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በስራ ቦታ እና ሰዓት ተገኝተው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ስለማድረጉ፤ /1%/

13.4. የትምህርት ቤቱ አመራር የተጠያቂነትን አሰራርና ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /1%/

ስታንዳርድ 14. የትምህርት ቤቱ ሃብት ለታቀደለት አላማ የፋይናንስ ህግን በመከተል ተተግብሯል፡፡ /2%/

አመልካች ፡-

14.1. የተሰበሰበውን የፋይናንስ ሀብት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ስለማዋሉ፤ /0.5%/

14.2. አመራሩ የትምህርት ቤቱን ቁሳቁስ እና መሰረተ ልማት በአግባቡ ስለማስተዳደሩ፤ /0.5%/

14.3. ለማህበረሰቡ በተቀመጠ ግንኙነት መሰረት የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርትን ለማህበረሰቡ ስለማሳወቅ /0.5%/

14.4. የትምህርት ቤቱ አመራር የንብረትና ፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /0.5%/

3.3. መማር ማስተማር /16%/

3.3.1. መማር /5%/

ስታንዳርድ15. የተማሪዎች የመማር ዝግጁነትና ተሳትፎ ጎልብቷል፤ /5%/

አመልካች ፡-

15.1. ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን አሟልተው ለትምህርት ዝግጁ ስለመሆናቸው፣ /0.5%/

15.2. ተማሪዎች በትምህርት ቤቱና በክፍል ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተው ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ስለመጠቀማቸው፣ /0.5%/

15.3. ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ የሚሰጡ ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በንቃት ስለመሳተፋቸው፤ /0.5%/

15.4. የተማሪዎች በክፍል ውስጥና ውጪ ጥያቄዎችን የመጠየቅና መልሶችን የመመለስ ተሳትፎ ስለማድረጋቸው፤ /1%/

15.5. ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ ስለማድረጋቸው፣ /0.5%/

15.6. ተማሪዎች አዲስ ነገር የመፍጠር፣ የመመራመርና የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ስለማድረጋቸው፣ /1%/

15.7. ተማሪዎች የስራና ተግባር ትምህርትን በሰርቶ ማሳያ ክፍል ስለመጠቀማቸው /1%/

3.3.2. ማስተማር /11%/

ስታንዳርድ 16. መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በአግባቡ ማቀዳቸው ተረጋግጧል፡፡ /2%/

አመልካች ፡-

16.1. የተማሪዎችን የትምህርት አቀባባል መሰረት በማድረግ መምህራን የትምህርት እቅድ /የትምህርቱን ዓላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ስነ- ዘዴን/ በማካተት በአግባቡ የተዘጋጀ ስለመሆኑ፤ /1%/

16.2. መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት የምዘና ዘዴ እና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በማካተት ስለማቀዳቸው፣ /1%/

ስታንዳርድ 17. መምህራን ተስማሚና አሳታፊ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን መጠቀማቸው ተረጋግጧል፡፡ /5%/

አመልካች ፡-

17.1. መምህራን ተማሪዎችን በጥንድ፣ በቡድን እና በግል እንዲረዳዱ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ስለመጠቀማቸው፤ /0.5%/

17.2. መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ቴክኖሎጂን (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር፣ ወዘተ ...) በመጠቀም ስለመስጠታቸው፤ /0.5%/

17.3. መምህራን ለሚያስተምሩት ትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ስለማዋላቸው፤ /0.5%/

17.4. መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ሳይንስ ኪት፣ ቤተ-ሙከራ ወዘተ... ስለመጠቀማቸው፤ /የስራና ተግባር ትምህርት /Workshop/ በመጠቀም የተግባር ተኮር ስልጠና ስለመስጠታቸው፤/ /0.5%/

17.5. መምህራን ተማሪዎቻቸው የአካባቢ ቁሳቁስ ተጠቅመው የፈጠራ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስራዎችን እንዲሰሩ ስለማበረታታቸው፤ /0.5%/

17.6. መምህሩ የተሻለ እውቀት፣ ልምድና ተሞክሮ ያላቸውን በመጋበዝ በመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲሳተፉ ስለማድረጉ፣ /0.5%/

17.7. መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ስለማካሄዳቸው፤ /1%/

17.8. መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት ይዘትንና ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦችን ለተማሪዎች በሚመጥን ቋንቋ በግልጽ አብራርተውና ቀለል አድርገው ስለማቅረባቸው፤ /1%/

ስታንዳርድ 18. መምህራን ተማሪዎችን በትክክል መመዘናቸው፣ ግብረ-መልስ መስጠታቸውና ድጋፍ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ /4/

አመልካች ፡-

18.1. መምህራን የሚተገብሩት ምዘና ስርዓተ-ትምህርቱን መሰረት ስለማድረጉና እና በፊተና ቢጋር /Table of Specifications/ ስለመዘጋጀቱ፣ /1/

18.2. መምህራን ተማሪዎችን በተቀመጠው ዝቅተኛ የመማር ብቃት /MLC/ መሠረት የንድፈ ሃሳብና የተግባር ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ የክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘናን ስለመስጠታቸው፤ /1/

18.3. መምህራን የተከታታይ የክፍል ውስጥ ምዘናን በመጠቀም ለተማሪዎች ወቅታዊ፣ ተዓማኒና ተገቢ ግብረ መልስ ስለመሰጠታቸው፤ /0.5%/

18.4. መምህራን የተማሪዎች ውጤት ትንተናን መሰረት በማድረግ ዝቅተኛ ውጤት ላላቸው ተጨማሪ ድጋፍ ስለማድረጋቸው፤ /1%/

18.5. መምህራን በየሴሚስተሩ አጋማሽ የተማሪዎችን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ-መልስ ስለመቀበላቸው፤ /0.5%/

3.3.3. **በትብብር መስራት /6%/**

ስታንዳርድ 19. መምህራን በጋራ የማቀድ፣ የመተግበርና የስርአተ ትምህርት ማቴርያሎችን መገምገምና ግብረ-መልስ መስጠታቸው ተረጋግጧል።። /3%/

አመልካች ፡-

19.1. መምህራን የሥርዓተ ትምህርት /ሰነዶችን/ ማቴርያሎችን በግልና በቡድን ገምግመው ግብረ-መልስ ስለመስጠታቸው፡/ 1%/

19.2. መምህራን በጋራ የማቀድና /Lesson study/፣ የመተግበር ስራዎችን ስለማከናወናቸው፤ /1%/

19.3. ከትምህርት ቤቶች ለት/ፅ/ቤት የተላኩ የመፅሀፍ ግምገማ አስተያየቶች ምላሽ እንዲያገኙ ስለመደረጉ፤ /1%/

ስታንዳርድ 20. የትምህርት ቤት አመራሮች እና መምህራን የሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብርን /CPD/ በአግባቡ ተግብረዋል።። /3%/

አመልካች ፡-

20.1. ለአዲስ ጀማሪ መምህራን የሙያ ትውውቅ /Induction Course/ ተግባራዊ ስለማድረጋቸውና ነባር መምህራን የሙያ ማሻሻያ መርሀ ግብርን /CPD/ ስለመተግበራቸው፤ /1.5%/

20.2. የት/ቤት አመራሮች የሙያ ማሻሻያ መርሀ ግብርን ተግባራዊ ስለማድረጋቸው፤ /1.5%/

3.4. የት/ቤት፣ የወላጅ እና ማህ/ሰብ ግንኙነትና አጋርነት /15%/

3.4.1. የትምህርት ቤት፣ የወላጅ እና የማህበረሰብ ግንኙነት /4%/

ስታንዳርድ 21. የትምህርት ቤት፣ የወላጅ እና የማህበረሰብ ግንኙነት የተጠናከረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /4%/

አመልካች ፡-

21.1. ትምህርት ቤቱ ከተማሪ ወላጆች ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ ስለመፍጠሩና ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /2%/

21.2. ወላጆች በት/ቤቱ በተቋቋሙ ኮሚቴዎች፣ አደረጃጀቶች እና መድረኮች በንቃት ስለመሳተፋቸው፣ /2%/

3.4.2. የትምህርት ቤት፣ የወላጆች ተሳትፎና የማህበረሰብ አጋርነት /11%/

ስታንዳርድ 22. ወላጆችና ማህበረሰቡ ለትምህርት ቤቱ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ /6%/

አመልካች ፡-

22.1. ወላጆች በገንዘብ፣ በአይነት፣ በእውቀትና በጉልበት ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ስለማድረጋቸው፤ /3%/

22.2. ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ ከቀድሞ ተማሪዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ ወዘተ... ሀብት (በገንዘብ፣ በአይነት፣ በእውቀትና በጉልበት) ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ስለማድረጋቸው፤ /3%/

ስታንዳርድ 23. ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተለያዩ ማህበራዊ አግልግሎቶችን መስጠቱ ተረጋግጧል፤ /2/

አመልካች ፡-

23.1. ትምህርት ቤቱ የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት የሚቻልበትን ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /1%/

23.2. ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ የመማማሪያ፣ የመመካከሪያ እና የልምድ መለዋወጫ ማዕከል ስለመሆኑ፤ /1%/

ስታንዳርድ 24. በትምህርትቤቱ የተማሪ ወላጆች በልጆቻቸው መማር ላይ ያላቸው ተሳትፎና /ሚና/ ማደጉ ተረጋግጧል፡፡ /3/

አመልካች ፡-

24.1. ወላጆች ለልጆቻቸው ውጤት መሻሻል ድጋፍ ስለማድረጋቸው፤ /0.5%/

24.2. ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲገኙ በአግባቡ ስለመከታተላቸው፤ /1%/

24.3. ወላጆች ለልጆቻቸው ባህሪ መሻሻል የድርሻቸውን ስለመወጣታቸው፤ /0.5%/

24.4. የተማሪ ወላጅ፣ መምህር ግንኙነት ስለመጠናከሩ፣ /1%/

3.5. ውጤት /20%/

3.5.1. ያደገ የትምህርት ተሳትፎ /13%/

ስታንዳርድ 25. ትምህርት ቤቱ ያቀደውን የትምህርትና ስልጠና ተሳትፎና ውስጣዊ ብቃት /internal efficiency/ አሳክቷል፡፡ /4.5%/

25.1. ትምህርት ቤቱ ያስቀመጠውን የተማሪ የቅበላ ዕቅድ ስለማሳካቱ፤ /1%/

25.2. ትምህርት ቤቱ የንጥር ተሳትፍ ምጣኔ ዕቅድን ስለማሳካቱ፤/1%/

25.3. ትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ጸታዊ ምጣኔ ዕቅድን ስለማሳካቱ፤/0.5%/

25.4. ትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ስለመቀነሱ፣ /0.5%/

25.5. ትምህርት ቤቱ መጠነ መድገም በዕቅዱ መሰረት ስለመቀነሱ፣/0.5%/

25.6. ትምህርት ቤቱ መጠነ ማርፈድ በእቅዱ መሰረት ስለመቀነሱ፣ /0.5%/

25.7. የትምህርት ቤቱ የማሳለፍ ምጣኔ ስለመጨመሩ፤ /0.5%/

3.5.2. የተሸሻለ የተማሪ ውጤት /8.5%/

ስታንዳርድ 26. ት/ቤቱ የተቀመጠውን የተማሪዎች ውጤት ግብ አሳክቷል /8.5/

አመልካች ፡-

26.1. ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ውጤታቸው 50% እና በላይ ስለመሆኑ፣ /1.5%/

26.2. ሁሉም ተማሪዎች በክልላዊ ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ውጤታቸው 50% እና በላይ ስለመሆኑ፤ /1.5%/

26.3. ሁሉም ተማሪዎች በሀገር ዓቀፍ ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ውጤታቸው 50% እና በላይ ስለመሆኑ፤/1.5%/

26.4. በትምህርትቤቱ ተከታታይነት ያለው የተሻሻለ የተማሪ ውጤት የማስመዝገብ ልምድ ስለመዳበሩ፤/1%/

26.5. ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ስለመሆኑ፤/1/

26.6. ትምህርት ቤቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ባደረገው ልዩ ድጋፍ በክፍል ፈተና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ውጤታቸው 50 ፐርሰንት እና በላይ ስለመሆኑ፤ /1%/

26.7. ሁሉም ሰልጣኞች በተግባር ፈተና በእያንዳንዱ በትምህርትና በሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍ ብቁ ስለመሆናቸው፤/1%/

3.5.3. የተሸሻለ የትምህርት ቤት ባህል /7%/

ስታንዳርድ 27. የተማሪዎች በራስ ጥረት የመስራት ባህል መዳበሩ ተረጋግጧል፡፡ /4%/

አመልካች ፡-

27.1. **ተማሪዎች በፈተና/በምዘና፣ የሚፈፀም ኩረጃ ፀያፍ መሆኑን ተገንዝበው አለመኮረጅን በተግባር ስለማሳየታቸው፤**/1%/

27.2. **በተማሪዎች መካከል በትምህርታቸው በበጎ ፈቃድ እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህል ስለመዳበሩ፤** /1%/

27.3. **የተማሪዎች የእርስ በርስ እና ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር የመከባበር ባህል ስለመዳበሩ፤** /1%/

27.4. **ተማሪዎች ሃሳባቸውን አደራጅተው የመግለፅና በራስ የመተማመን ልምዳቸው ስለመጎልበቱ፤** /1%/

ስታንዳርድ 28. በትምህርትቤቱ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያላቸው እሴቶች መጎልበታቸው ተረጋግጧል፡፡/3%/

አመልካች ፡-

28.1. **በትምህርት ቤቱ የተዘጋጀው መተዳደሪያ ደንብ አጋዥነት ሰላማዊ የስራ አካባቢ ስለመፈጠሩ፤**/1%/

28.2. **በትምህርት ማህበረሰቡ /መምህራን፣ ር/መ/ራን፣ አስተዳደር ሰራተኞችና ተማሪዎች/ የመረዳዳት የመቻቻል የመከባበር ባህል ስለመዳበሩ፤** /1%/

28.3. **ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ስለመንከባከባቸው፣** /1%/

ግላጮች /Descriptors/

በውሳኔ አሰጣጥ /ደረጃ ምደባ ሂደት ላይ ውሳኔ ሰጪው አካል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተገንዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡

እንደ አጠቃላይ በዚህ ሰነድ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉና በአተረጓጎም ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ታስቦ በመስፈርትነት የተቀመጡ ቃላቶች ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

- ከፍተኛ እጥረት፣ በጣም ዝቅተኛ፣ አነስተኛ፣ ውሱን፣ ጥቂት ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር ከ50 በመቶ በታች ያገኝ፣
- አብዛኛው /አብዛኞቹ/ ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር 50-69.99 በመቶ ያገኘ፣
- ሙሉ በሙሉ /ሁሉንም ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ 70 በመቶ በላይ ያገኘ፣

በሚል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

1. ግብዓት 20%

1.1 ምቹ የመማሪያ አካባቢ

1.1.1. የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ እና መሰረተ ልማት /8%/

ስታንዳርድ 1 .በትምህርት ቤቱ በስታንዳርድ መሰረት የቦታ ስፋት፣ የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች እና ቦታዎችን መኖራቸው ተረጋግጧል። /5%/				
ተ.ቁ	አመላካቾች	ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
1.1.	ትምህርት ቤቱ ተፈላጊውን የቦታ ስፋትና የይዞታ ማረጋገጫ ስለማሟላቱ፤ /0.5/	ትምህርት ቤቱ ከተቀመጠው የት/ቤቶች ስታንዳርድ መሰረት 50 ከመቶ በታች የቦታ ስፋት አሟልቷል፣	ትምህርት ቤቱ ከተቀመጠው የት/ቤቶች ስታንዳርድ አንጻር 50-69.99 በመቶ የቦታ ስፋት አሟልቷል፣	ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው የት/ቤቶች ስታንዳርድ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣
1.2.	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት (ቤተ-መፅሃፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ) መሰረተ ልማቶች በስታንዳርዱ መሰረት የታነፁ ስለመሆናቸው፣ /1%/	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት ተፈላጊውን መ ሰረተ ልማት በከፊል አሟል ቷል፣	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት ተፈላጊውን መሰረተ ልማት በአብዛኛው አሟልቷል፣	ትምህርት ቤቱና የአካባቢ ው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት ተፈላጊውን መሰረተ ልማት ሙሉ በሙሉ ተሟልቷል፣
1.3.	በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባራት የሚካሄድባቸው መሰረተ ልማቶች (መማሪያ ክፍሎች፣	በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባር የሚካሄድበት ተፈላጊውን መሰረተ ልማት በከፊል አሟ	በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባር የሚካሄድበ ት ተፈላጊውን መሰረተ ልማት በአብዛኛው	በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባር የሚካሄድ በት ተፈላጊውን መሰረተ ልማት

	የመምህራን ማረፊያና አስተዳደር ቢሮዎች፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወዘተ...) በስታንዳርዱ መሰረት የታነፁ ስለመሆናቸው፣ /1%/	ልቷል፣	ተሟልቷል፣	ሙሉ በሙሉ ተሟልቷል፣
1.4.	በትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ ጋር ስለመሟላቱ፣ /0.5/	በትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ተሟልቷል	በትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁ በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ ጋር ስለመሟላቱ፣	በትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የተማሪዎች፣ የመምህራንና ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ ጋር ስለመሟላቱ፣
1.5.	ትምህርት ቤቱ በቂ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት ስለመኖሩ፣ /0.5/	በትምህርት ቤቱ የሚገኘውን የመጠጥ የውሃ አቅርቦት አልፎ አልፎ ይጠቀማሉ፣	ትምህርት ቤቱ አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው፣	ትምህርት ቤቱ በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋለ በቂ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው፣
1.6.	ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል መሰረተ ልማቶች (ለእርሻና ለእርባታ ቦታዎች፣ ለእድ ጥበብ መስሪያ) በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የታነፁ ስለመሆናቸው፣ /1/	በትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል መሰረተ ልማት በከፊል ተሟልቷል፣	በትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል መሰረተ ልማት በአብዛኛው ተሟልቷል፣	በትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል መሰረተ ልማት በአብዛኛው ተሟልቷል፣
1.7.	ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች	ትምህርት ቤቱ ለስራና ተግባር ትምህርቶች በተቀመጠው	ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የስራና	ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የስራና

	የስራና ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ የትምህርት ማሰልጠኛ የሚያገለግል (ለማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ፣ ለህንፃ ግንባታ ቴክኖሎጂ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ለግብርና ሳይንስ፣ ለጤና ሳይንስ፣ ለተግባቦትና ማህበራዊ ሳይንስ፣ ለቢዝነስ ሳይንስ፣ ለክዋኔና ለትዕይንት ማቅረቢያ ወዘተ) መሰረተ ልማቶች የታነፁና ናቸው፡፡ /0.5/	ስታንዳርድ መሰረት የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ ከአስፈላጊው መሰረተ ልማት ከ50% በታች ነው፡፡	ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ የትምህርት ማሰልጠኛ የሚያገለግል መሰረተ ልማቶች በአብዛኛው የታነፁ ናቸው፡፡	ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ የትምህርት ማሰልጠኛ የሚያገለግል መሰረተ ልማቶች ሙሉ በሙሉ የታነፁ ናቸው፡፡

ስታንዳርድ 2. ትምህርት ቤቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለመማሪያ፣ ለአገልግሎት መስጫ ክፍሎች እና ቦታዎች የሚያገለግሉ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን /ግብዓቶችን/ መሟላታቸው ተረጋግጧል፡፡ /3%/

ተ.ቁ	አመላካቾች	ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
2.1	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት (ቤተ-መፅሃፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ) በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቁሳቁሶችን ስለመሟላቱ፣ /0.5%/	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት የቦታና ክፍል ቁሳቁሶች በከፊል ተሟልቷል፣	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት የቦታና ክፍል ቁሳቁሶች በአብዛኛው ተሟልቷል፣	ትምህርት ቤቱና የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገሉበት የቦታና ክፍል ቁሳቁሶች ሙሉ በሙሉ ተሟልቷል፣
2.2	ት/ቤቱ የመማሪያ፣ የቤተ-ሙከራዎች፣ የመምህራን ማረፊያ፣ መመገቢያ አዳራሽ እና አስተዳደር ክፍሎችን ከአስፈላጊ ቁሳቁሶች ጋር ስለማማላቱ፣ /1%/	ት/ቤቱ የመማሪያ፣ የቤተ-ሙከራዎች፣ የመምህራን ማረፊያና አስተዳደር ክፍሎችን አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በከፊል ተሟልቷል፣	ት/ቤቱ የመማሪያ፣ የቤተ-ሙከራዎች፣ የመምህራን ማረፊያና አስተዳደር ክፍሎችን አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በአብዛኛው ተሟልቷል፣	ት/ቤቱ የመማሪያ፣ የቤተ-ሙከራዎች፣ የመምህራን ማረፊያና አስተዳደር ክፍሎችን አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ሙሉ በሙሉ ተሟልቷል፣

2.3	ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል (የእርሻና የእርባታ ቦታዎች፣ የእድ ጥበብ ሰርቶ ማሳያዎች የእንጨትና ብረታ ብረት ስራ ቦታዎችን ወዘተ) ቁሳቁሶችን /ግብዓቶችን/ ስለመሟላቱ፡፡ /1%/	በትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል ቦታና ክፍሎች ቁሳቁስ /ግብዓት/ በከፊል ተሟልቷል፣	በትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል ቦታና ክፍሎች ቁሳቁስ /ግብዓት/ በአብዛኛው ተሟልቷል፣	በትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ለሰርቶ ማሳያ የሚያገለግል ቦታና ክፍሎች ቁሳቁስ /ግብዓት/ ሙሉ በሙሉ ተሟልቷል፣
2.4	ትምህርት ቤቱ ተግባራዊ እያደረገ ለሚገኝባቸው ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የስራና ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ (ለማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ፣ ለህንፃ ግንባታ ቴክኖሎጂ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ለግብርና ሳይንስ፣ ለጤና ሳይንስ፣ ለተግባቦትና ማህበራዊ ሳይንስ፣ ለቢዝነስ ሳይንስ፣ ለክዋኔና ለትዕይንት ማቅረቢያ ወዘተ) የማሰልጠኛ አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች ጋር ስለመሟላቱ፣ /0.5%/	ትምህርት ቤቱ ተግባራዊ እያደረገ ለሚገኝባቸው የስራና ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ የሚያገለግል የማስተማሪያ ወይም የማሰልጠኛ ቁሳቁሶች ከ50% በታች ነው፣	ትምህርት ቤቱ ተግባራዊ እያደረገ ለሚገኝባቸው የስራና ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ የሚያገለግል የማስተማሪያ ወይም የማሰልጠኛ ቁሳቁሶች በአብዛኛው የተሟሉ ናቸው፣	ትምህርት ቤቱ ተግባራዊ እያደረገ ለሚገኝባቸው የስራና ተግባር ትምህርቶች የተግባር ስራ የሚሰራበት ሰርቶ ማሳያ /Workshop/ የሚያገለግል የማስተማሪያ ወይም የማሰልጠኛ ቁሳቁሶች ሙሉ በሙሉ የተሟሉ ናቸው

1.1.2. ምቹ አካባቢ /4%/

ስታንዳርድ 3፡ የትምህርት ቤቱ ውስጥና ውጫዊ አካባቢ ምቹና ደህንነቱ የማያሰጋ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /2%/				
አመላካቾች		ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 (አጥጋቢ)	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
3.1	በት/ቤቱ የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለሁሉም ተማሪዎች ምቹ ስለመሆናቸው፤ /1%//	በት/ቤቱ የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በከፊል ምቹ ናቸው፤	በት/ቤቱ የሚገኙ ለአብዛኛው የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ተማሪዎች ምቹ ናቸው፤	በት/ቤቱ የሚገኙ ሁሉም የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ተማሪዎች ምቹ ናቸው፤
3.2	የትምህርት ቤቱ አካባቢ ከአዋኪ ጉዳዮች የጸዳ ስለመሆኑ፤ /1%/	የትምህርት ቤቱ አካባቢ በውስን ደረጃ ከአዋኪ ጉዳዮች የጸዳ ነው፡፡	የትምህርት ቤቱ አካባቢ ከአዋኪ ጉዳዮች በአብዛኛው የጸዳ ነው፡፡	የትምህርት ቤቱ አካባቢ ከአዋኪ ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ የጸዳ ነው፡፡
ስታንዳርድ 4. ት/ቤቱ ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው እና ለሴት ተማሪዎች ምቹ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /2/				
4.1	ትምህርት ቤቱ ልዩ የመማር ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ፤ /1/	ትምህርት ቤቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በውስን ደረጃ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፤	ትምህርት ቤቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በአብዛኛው ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፤	ትምህርት ቤቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፤
4.2	ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ፡ /1/	ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች የሚሆን የግል መጠበቂያ ክፍሎች ቢኖሩትም በቁሳቁስ አልተሟላም፤	ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች የሚሆን የግል መጠበቂያ ክፍሎች እና በአስፈላጊ ቁሳቁስ የተሟላ ነው፤	ትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች የሚሆን የግል ንፅህና መጠበቂያ ክፍል ከሻወር ጋር አሟልቷል፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ ቁሳቁሶችንም በማሟላት ምቹ

				ሁኔታ ፈጥሯል፤

1.1.3. ፋይናንስና የሰው ሃይል /8%/

ስታንዳርድ 5. ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ላቀዳቸው ተግባራት የፋይናንስ ሀብት አሰባስቧል፤ /3/				
አመላካቾች		ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
5.1	ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ ሀብት የሚያሰባስብበት እቅድ ስለማዘጋጀቱ፤ /1%/	ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀው እቅድ ከውስጥ ገቢ ብቻ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው፤	ትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡን በማሳተፍ ከውስጥ ገቢ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ከመንግስታዊ ተቋማት ሀብት ለመሰብሰብ አቅዷል ፤	ትምህርት ቤቱ ማህበረሰቡን በማሳተፍ ከውስጥ ገቢ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ሀብት ለመሰብሰብ አቅዷል፤
5.2	በእቅዱ መሰረት ሀብት ስለማሰባሰቡ፣ /1%/	ትምህርት ቤቱ ከእቅዱ 50% በታች ሀብት አሰባስቧል፤	ትምህርት ቤቱ ከእቅዱ 50-69.99% ሀብት አሰባስቧል፤	ትምህርት ቤቱ ከእቅዱ 70% በላይ ሀብት አሰባስቧል፤
5.3	በእቅዱ መሰረት ፕሮጀክት በመቅረፅ ሀብት ስለማሰባሰቡ፣ /0.5%/	ትምህርት ቤቱ ከእቅዱ 50% በታች ከተማሪ ወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ ... ፕሮጀክት በመቅረፅ ሀብት አሰባስቧል፡፡	ትምህርት ቤቱ ከእቅዱ 50-69.99% ከተማሪ ወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ ... ፕሮጀክት በመቅረፅ ሀብት አሰባስቧል፡፡	ትምህርት ቤቱ 70% በላይ ከተማሪ ወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ ... ፕሮጀክት በመቅረፅ ሀብት አሰባስቧል፡፡

5.4	በወረዳው / ከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊውን በጀት ስለመመደቡ፤ /0.5%/	የጥቅል በጀት /BLOCK GRANT እና ወይም ድጎማ በጀት /SCHOOL GRANT ከ50% በታች መድቧል፤	ጥቅል በጀት /BLOCK GRANT እና ወይም ድጎማ በጀት /SCHOOL GRANT ከ50% በላይ መድቧል፤	ጥቅል በጀት /BLOCK GRANT እና ወይም ድጎማ በጀት /SCHOOL GRANT ሙሉ በሙሉ መድቧል፤
ስታንዳርድ 6. በትምህርት ቤቱ የትምህርት ቤት አመራር፣ መምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ተሟልቷል፡፡ /4%/				
6.1	ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ስለማሟላቱ፤ /1%/	ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን በከፊል አሟልቷል፡	ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን በአብዛኛው አሟልቷል፡	ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ሙሉ በሙሉ አሟልቷል፡
6.2	ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው የትምህርት ቤት አመራሮች ስለማሟላቱ፤ /1%/	ት/ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ዝግጅት ያላቸው የትምህርት ቤት አመራሮች በከፊል አሟልቷል፣	ት/ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ዝግጅት ያላቸው የትምህርት ቤት አመራሮች በአብዛኛው አሟልቷል፣	ት/ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ዝግጅት ያላቸው የትምህርት ቤት አመራሮች ሙሉ በሙሉ አሟልቷል፣
6.3	ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥን የአስተዳደር ሰራተኞችን ስለማሟላቱ፤ /1%/	ትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ሰራተኞችን በስታንዳርዱ መሰረት በከፊል አሟልቷል፤	ትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ሰራተኞችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አሟልቷል፣	ትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ሰራተኞችን በስታንዳርዱ መሰረት ሙሉ በሙሉ አሟልቷል፤
6.4	ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው መሰረት ተማሪዎችን የመደልደል ስራ አከናውኗል ፤ /1%/	ትምህርት ቤቱ ለደረጃው ከተቀመጠው በላይ ተማሪዎችን የመደልደል ስራ አከናውኗል ፤	ትምህርት ቤቱ በአብዛኛው ለደረጃው የተቀመጠውን ስታንዳርድ በማሟላት ተማሪዎችን ደልድሏል፤	ትምህርት ቤቱ ሙሉ በሙሉ ለደረጃው የተቀመጠውን ስታንዳርድ በማሟላት ተማሪዎችን ደልድሏል፤
ስታንዳርድ 7. አመራሩ አሳታፊ የትምህርት ቤት መሻሻል እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ /1/				

7.1	አመራሩ የትምህርት ቤት ግለ ግምገማ እንዲካሄድ ስለማድረጉ፣ /0.5%/	አመራሩ የትምህርት ቤት ግለግምገማ ለማካሄድ ኮሚቴ አቋቁሟል፣	አመራሩ የትምህርት ቤት ግለ ግምገማ ለማካሄድ ኮሚቴ አቋቁሞ መረጃ ሰብስቧል	አመራሩ የትምህርት ቤት ግለ ግምገማ አካሂዷል።
7.2	የሦስት ዓመት ስትራቴጂክ እና አመታዊ የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ ከግለ ግምገማና ኢንስፔክሽን ግብረ-መልስ በመነሳት ባለድርሻ አካላትን አሳትፎ ስለማዘጋጀቱ፣ /0.5/	አመራሩ የሦስት ዓመት ስትራቴጂክ እና አመታዊ የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ አላዘጋጀም	አመራሩ የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ አስገብቷል፣ አፈፃፀሙን በቸክሊስት ተከተትሏል፣ ወቅታዊ ግምገማ አካሂዷል፣	አመራሩ የተዘጋጀውን የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ወደ ትግበራ አስገብቶ አፈፃፀሙን በቸክሊስት ተከተትሏል፣ ወቅታዊ ግምገማ አካሂዷል፣ የሚሻሻሉ ጉዳዮችን በመለየት የማስተካከያ ርምጃዎችን ወስዷል፣

2. ሒደት (60%)

2.1. የትምህርትቤት አመራርና አስተዳደር /35%/

2.1.1. የመምራት ብቃት /10%/

ስታንዳርድ 8. አመራሩ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋት፣ የለውጥ እና የህዝብ ግንኙነት ሥራን በአግባቡ የመምራት ክህሎት አድጓል፤/4%/				
አመላካቾች		ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
8.1	ከትምህርት ቤት መሻሻል ጋር ተያይዘው የሚመጡ የለውጥ ስራዎችን በአግባቡ ስለመምራቱ፤ /1%/	ከትምህርት ቤት መሻሻል ጋር ተያይዘው የሚመጡ የለውጥ ስራዎች ተቀብሎ የእቅድ አካል አድርጓል፣	ከትምህርት ቤት መሻሻል ጋር ተያይዘው የሚመጡ የለውጥ ስራዎችን የእቅድ አካል አድርጎ በአግባቡ የመገምገምናየመምራት ስራ ሰርቷል፤	ከትምህርት ቤት መሻሻል ጋር ተያይዘው የሚመጡ የለውጥ ስራዎችን የእቅድ አካል አድርጎ በአግባቡ የመገምገምና የመምራት ስራ በመስራት ውጤት አስመዝግቧል፣
8.2	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በወቅቱ የማስተዋወቅ ተግባር ስለማከናወኑ፤ /1%/	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ አላስተዋወቀም፣	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ የማስተዋወቅ	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ የማስተዋወቅ

			ስራ ሰርቷል፣	ስራ በመስራት የተሰጡ ግብረ-መልሶችና ውጤቶች በመረጃ ተይዟል፤
8.3	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ ያሉ እና ከሌሎች የተገኙ መልካም ልምዶችን፣ ዕውቀቶችንና ተሞክሮዎችን ቀምሮ ተግባራዊ ስለማድረጉ፣ /1% /	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ ያሉ እና ከሌሎች የተገኙ መልካም ልምዶችን፣ ዕውቀቶችንና ተሞክሮዎችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፣	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ ያሉ እና ከሌሎች የተገኙ መልካም ልምዶችን፣ ዕውቀቶችንና ተሞክሮዎችን ለይቶ ሰነድ አዘጋጅቷል፤	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ ያሉ እና ከሌሎች የተገኙ መልካም ልምዶችን፣ ዕውቀቶችንና ተሞክሮዎችን ለይቶ በመቀመር ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አድርጓል፤
8.4	አመራሩ እና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፉ የተደገፉ የአሰራር ስርዓት ስለመፍጠሩ፤ /1%/	አመራሩ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን በቴክኖሎጂ የተደገፉ የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋም ተግባራዊ አላደረገም።	አመራሩ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን በቴክኖሎጂ የተደገፉ የአሰራር ስርዓት ፊጥሮ በአብዛኛው ተግባራዊ አድርጓል።	አመራሩ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን በቴክኖሎጂ የተደገፉ የአሰራር ስርዓት ፊጥሮ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በማድረግ ውጤት አስመዝግቧል።
ስታንዳርድ 9. የትምህርት ቤቱ የአመራር የራሱን፣ የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኛውን ሙያዊ ክህሎት ለማዳበር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስልጠና አዘጋጅቶ ተግባራዊ አድርጓል።። /3/				
ተ.ቁ	አመላካቾች	ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
9.1	አመራሩ የራሱንና የመምህራን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችልየአቅም ግንባታ መርሃ ግብር አውጥቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ፣ /1%/	አመራሩ የራሱን፣ የመምህራንን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል፤	አመራሩ የራሱንና የመምህራን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል አዳዲስ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቷል፤	አመራሩ የራሱንና የመምህራን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል አዳዲስ የአሰራር ሥርዓቱን

				ተግባራዊ አድርጓል፤
9.2	የአስተዳደር ሰራተኞችን ሙያዊ ክህሎት የማሻሻያ ተግባራት ስለማከናወኑ፣ /1%/	አመራሩ የአስተዳደር ሰራተኞችን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል፤	አመራሩ የአስተዳደር ሰራተኞችን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል አዳዲስ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቷል፤	አመራሩ የአስተዳደር ሰራተኞችን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስችል አዳዲስ የአሰራር ሥርዓቱን ተግባራዊ አድርጓል፤
9.3	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ ስለማግኘቱ፣ /1%/	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር የሚገናኝበት የትስስር እቅድ አለው፤	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ግንኙነት ጀምሯል፤	የትምህርት ቤቱ አመራር በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ አግኝቷል፤
ስታንዳርድ 10. የትምህርት ቤቱ አመራር የልዩ ልዩ አደረጃጀት ተጠሪዎች የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መተግበራቸውን አረጋግጧል፡፡ /4%/				
10.1	የት/ቤቱ አመራር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን በማደራጀት ተግባርና ሃላፊነታቸውን ስለማውረዱ፤ /0.5/	አመራሩ ለምክትል ርዕሰ መምህራን ብቻ ተግባርና ኃፊነት ሰጥቷል፤	አመራሩ ለአብዛኛው በየደረጃው ላሉ አካላት ተግባርና ኃፊነት ሰጥቷል፤	አመራሩ በየደረጃው ላሉ ለሁሉም አካላት (ለምክትል ርዕሰ መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች፣ መምህራን፣ ለኮሚቴዎች፣ ለአስተዳደር ሠራተኞች...) ተግባርና ኃፊነት ሰጥቷል፤

10.2	የት/ቤቱ አመራር ለአደረጃጀቶች የሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነት አፈጻጸም በየወቅቱ ስለመደገፉ፤ ስለመከታተሉና ግብረ-መልስም ስለመስጠቱ፤ /1.5/	አመራሩ በየደረጃው በሰጠው ተግባርና ኃፊነት መሠረት በከፊል ለመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ክትትል አድርጓል፤ ሪፖርት ተቀብሏል፤ ግብረመልስ ሰጥቷል፡፡	አመራሩ በየደረጃው በሰጠው ተግባርና ኃፊነት መሠረት ለአብዛኛው መምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ክትትል አድርጓል፤ ሪፖርት ተቀብሏል፤ ግብረመልስ ሰጥቷል፡፡	አመራሩ በየደረጃው በሰጠው ተግባርና ኃፊነት መሠረት ለሁሉም አካላት ክትትል አድርጓል፤ ሪፖርት ተቀብሏል፤ ግብረመልስ ሰጥቷል፡፡
10.3	የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴን የእቅድ አፈፃፀሞች ስለመከታተሉ፤ ስለመደገፉና ግብረ-መልስ ስለመስጠቱ፤ /1%/	አመራሩ የት/ቤቱ አመራረዉ የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴን እቅድ አፈፃፀሞች ይከታተላል፤	የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴን እቅድ አፈፃፀሞች ስለመከታተሉ፤ ይደግፋል	የትምህርት ቤት መሻሻል ኮሚቴን እቅድ አፈፃፀሞች ስለመከታተሉ፤ ስለመደገፉና ግብረ-መልስ ስለመስጠቱ፤
10.4	በትምህርት ቤቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት አመራሩ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያሳትፍ ስርዓት ስለመዘርጋቱ፤ /0.5%/	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብን አልፎ አልፎ ያሳትፋል፤	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት በአብዛኛው የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብን የሚያሳትፍ ስርዓት ዘርግቷል፤	በትምህርት ቤቱ አመራር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የሚያሳትፍ ስርዓት ዘርግቷል፤

2.1.2. የማስተማር ሂደት እና ተነሳሽነት /11%/

ስታንዳርድ 11. በትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ተፈጥሯል።። /4 /				
አመላካቾች		ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
11.1	አመራሩ የውስጥ ሱፐርቪዥን ስርዓት በመዘርጋት ለመምህራን ሙያዊ ድጋፍ ስለመስጠቱ፤ /1%/	አመራሩ በአመት አንድ ጊዜ ለሚሆኑት መምህራን የውስጥ ሱፐርቪዥን በማካሄድ ግብረ-መልስ ሰጥቷል፣	አመራሩ ለሁሉም መምህራን በአመት ሁለት ጊዜ ጊዜ ለአብዛኛው መምህራን የውስጥ ሱፐርቪዥን አካሂዶ ግብረ-መልስም ሰጥቷል፣	አመራሩ ለሁሉም መምህራን በአመት ሶስት ጊዜ የውስጥሱፐርቪዥን አካሂዷ ል፣ ግብረ-መልስም ሰጥቷል፣
11.2	መምህራን እርስ በእርሳቸው የክፍል ውስጥ ምልከታ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ፤ /1%/	ለመምህራን የእርስ በርስ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለማድረግ የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶቷል፣	ለመምህራን የእርስ በርስ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለማድረግ የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶቷል፣ የአፈፃፀም ክትትል አድርጓል፣	ለመምህራን የእርስ በርስ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለማድረግ የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶቷል፣ ክትትል አድርጓል፣ አፈፃፀሙንም ገምግሟል፣ በተገኙ ግኝቶች ላይ ድጋፍ አድርጓል
11.3	መምህራን ለተማሪዎች ተከታታይ ምዘና እና ግብረ-መልስ መስጠታቸውን ስለመደገፉና ስለመከታተሉ፤ /1%/	አመራሩ ለጥቂት መምህራን የተከታታይ ምዘና ማካሄዳቸውን እና ግብረመልስ መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ግብረመልስ ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣	አመራሩ ለአብዛኛዎቹ መምህራን የተከታታይ ምዘና ማካሄዳቸውን እና ግብረመልስ መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ግብረመልስ ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣	አመራሩ ሁሉም መምህራን የተከታታይ ምዘና ማካሄዳቸውን እና ግብረመልስ መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ግብረመልስ ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣

11.4	የመምህራን እና የተማሪዎችን የአመራር ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /1%/	አመራሩ የመምህራንና የተማሪዎችን የአመራር ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት አልዘረጋም፤	አመራሩ የመምህራንና የተማሪዎችን የአመራር ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቷል፣ ነገር ግን ተግባራዊ አላደረገም	አመራሩ የመምህራንና የተማሪዎችን የአመራር ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችሉ የክርክር መድረኮች፣ የፓናል ውይይቶችን፣ የውይይት መድረኮች በማመቻቸት ተሰጥኦአቸውን እንዲያወጡ የሚያደርጉ አደረጃጀቶችን እና አሰራር በመፍጠር ተግባራዊ አድርጓል፣
ስታንዳርድ 12. በትምህርትቤቱ አመራር የመምህራን የማስተማር ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት መፈጠሩ ተረጋግጧል፡፡/4/				
ተ.ቁ	አመላካቾች	ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
12.1	የት/ቤቱ አመራር ስኬታማ ግለሰቦችን በመጋበዝ ሙያዊ ተሞክሮዎችን እንዲያካፈሉ ስለማድረጉ፤ /1%/	አመራሩ ስኬታማ ግለሰቦችን በመጋበዝ ሙያዊ ተሞክሮዎችን እንዲያካልፍሉ ልየታ አካሂዷል	አመራሩ ስኬታማ ግለሰቦችን በመጋበዝ ሙያዊ ተሞክሮዎችን እንዲያካፍሉ ልየታ አካሂዷል፣ የተሞክሮ ማካፈያ መርሀግብር አዘጋጅቷል	አመራሩ ስኬታማ ግለሰቦችን በመጋበዝ ሙያዊ ተሞክሮዎችን እንዲያካፍሉ፣ተደርጓል፣

12.2	ለመምህራን ምቹ የስራ አካባቢ ስለመፈጠሩ፤ /1%/	አመራሩ ለመምህራን ምቹ የስራ አካባቢ ለመፍጠር የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን አጠናቋል።	ለአብዛኛዎቹ መምህራን ምቹ የስራ አካባቢ ተፈጥሯል፤ የማረፊያ ክፍሎች ንፅህና ተጠብቋል፤ አስፈላጊ ቁሳቁሶች ተሟልተዋል፤	ለሁሉም መምህራን ምቹ የስራ አካባቢ ተፈጥሯል፤ የማረፊያ ክፍሎች ንፅህና ተጠብቋል፤ አስፈላጊ ቁሳቁሶች ተሟልተዋል፤ በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ መዝናኛና አገልግሎት መስጫ ክፍሎችና ቦታዎች ተሟልተዋል፤ የመምህራን የስራ እርካታ ከ70% በላይ ሆኗል፤
12.3	የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው መምህራን የሚበረታቱበት ግልፅ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ፤ /1%/	የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን መምህራንን ለማበረታታት ስርዓት ተዘርግቷል	የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን መምህራንን በከፊል የማበረታታት ስራ ተጀምሯል፤	ትምህርት ቤቱ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው መምህራንን በተከታታይነት ያበረታታል፤ አቅምን ያገናዘበ ሽልማት ይሸልማል።
12.4	የት/ቤቱ አመራር ሁሉም መምህራን በእኩልነት /በውሳኔ ሰጭነት/ የሚሳተፉበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፤ /1%/	አመራሩ አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራር ለመተግበር የሚያስችል ስርኣት ዘርግቷል፤	አመራሩ መምህራን በተለያዩ ስራዎች እና የውሳኔ ሰጪነት ሚናዎች ላይ እኩል የሚሳተፉበትን ስርዓት ዘርግቷል። ከሞላ ጎደል ተግባራዊ ያደርጋል።	አመራሩ በትምህርት ቤት ሁሉም መምህራን በእኩልነት የሚሳተፉበትን ስርዓት ዘርግቷል። ተግባራዊም አድርጓል።

2.1.3. የት/ቤት አስተዳደር /5%/

ስታንዳርድ 13. የትምህርት ቤቱ አመራር መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞችን በአግባቡ በመመደብ ተግባርና ሀላፊነታቸውን መወጣታቸውን መከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፤ /3%/				
አመላካቾች		ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
13.1	ሁሉም መምህራን በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ ስለመደረጉ፤ /0./5%/	ጥቂት መምህራን በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ አድርጓል	አብዛኛውን መምህራን በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ አድርጓል	ሁሉም መምህራን በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ አድርጓል
13.2	ሁሉም የአስተዳደር ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ ስለመደረጉ፤ /0.5%/	ጥቂት የአስተዳደር ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ አድርጓል	አብዛኛውን መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ አድርጓል	ሁሉም መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በሰለጠኑበት የሙያ መስክ እንዲመደቡ አድርጓል
13.3	የትምህርት ቤቱ አመራር መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በስራ ቦታ እና ሰዓት ተገኝተው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ስለማድረጉ፤ /1%/	የትምህርት ቤቱ አመራር ከ50% በታች የሚሆኑ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በስራ ቦታ እና በሰዓቱ ተገኝተው	የትምህርት ቤቱ አመራር አብዛኛው መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በስራ ቦታ እና በሰዓቱ ተገኝተው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ	የትምህርት ቤቱ አመራር ሁሉም መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች በስራ ቦታ እና በሰዓቱ ተገኝተው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ

		ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አድርጓል፤	አድርጓል	አድርጓል
13.4	የትምህርት ቤቱ አመራር የተጠያቂነትን አሰራርና ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /1%/	አመራሩ በትምህርት ቤቱ የተጠያቂነት ስርዓት ዘርግቷል፤	አመራሩ በአብዛኛው በትምህርት ቤቱ የተጠያቂነት ስርዓት በማስፈን ውጤታማ ሆኗል፤	አመራሩ ሙሉ በሙሉ በትምህርት ቤቱ የተጠያቂነት ስርዓት በማስፈን ውጤታማ ሆኗል፤
ስታንዳርድ 14. የትምህርት ቤቱ ሃብት ለታቀደለት አላማ የፋይናንስ ህግን በመከተል ተተግብሯል፡፡ /2%/				
1.ቁ	አመላካቾች	ደረጃ 1 ዝቅተኛ	ደረጃ 2 አጥጋቢ	ደረጃ 3 ስታንዳርዱን ያሟላ
14.1	የተሰበሰበውን የፋይናንስ ሀብት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት ስለማዋሉ፤ /0.5%/	በት/ቤቱ የተሰበሰበውን የፋይናንስ ሀብት በከፊል ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፡፡	የተሰበሰበውን የፋይናንስ ሀብት በአብዛኛው ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፡፡	የተሰበሰበውን የፋይናንስ ሀብት ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፡፡
14.2	አመራሩ የትምህርት ቤቱን ቁሳቁስ እና መሰረተ ልማት በአግባቡ ስለማስተዳደሩ፤ /0.5%/	አመራሩ የትምህርት ቤቱን ቁሳቁስ እና መሰረተ ልማት በከፊል አስተዳድሯል፤	አመራሩ የትምህርት ቤቱን ቁሳቁስ እና መሰረተ ልማት በአብዛኛው አስተዳድሯል፤	አመራሩ የትምህርት ቤቱን ቁሳቁስ እና መሰረተ ልማት ሙሉ በሙሉ በአግባቡ አስተዳድሯል፤
14.3	በተቀመጠ ግንኙነት መሰረት የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርትን ለማህበረሰቡ ስለማሳወቅ /0.5%/	ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርትን በአመት አንድ ጊዜ ለማህበረሰቡ አሳውቋል፤	ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርትን በአመት ሁለት ጊዜ ለማህበረሰቡ አሳውቋል፤	ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርትን በአመት ሶስት ጊዜ ለማህበረሰቡ አሳውቋል፤
14.4	የትምህርት ቤቱ አመራር የንብረትና ፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ፤ /0.5%/	የትምህርት ቤቱ አመራር የንብረትና ፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት አልዘረጋም፤	የትምህርት ቤቱ አመራር የንብረትና ፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቷል፤	የትምህርት ቤቱ አመራር የንብረትና ፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ

				አድርጓል፣

2.2. መማር ማስተማር //

2.2.1. መማር /5%/

ስታንዳርድ 15 :- የተማሪዎች የመማር ዝግጁነትና ተሳትፎ ጎልብቷል፤ /5%/				
አመላካቾች		ደረጃ 1 (ዝቅተኛ) (1)	ደረጃ 2 (አጥጋቢ) (2)	ደረጃ 3 (ስታንዳርዱን ያሟላ) (3)
15.1.	ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን አሟልተው ለትምህርት ዝግጁ ስለመሆናቸው፣ /0.5%/	ጥቂት ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን አሟልተው ለትምህርት ዝግጁ ሆነዋል፣	አብዛኛው ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን አሟልተው ለትምህርት ዝግጁ ሆነዋል፣	ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን አሟልተው ለትምህርት ዝግጁ ሆነዋል፣
15.2.	ተማሪዎች በትምህርት ቤቱና በክፍል ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተው ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ስለመጠቀማቸው፣ /0.5%/	የተወሰኑ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱና በክፍል ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተው ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣	አብዛኛው ተማሪዎች በትምህርት ቤቱና በክፍል ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተው ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣	ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤቱና በክፍል ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተው ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣
15.3.	ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ የሚሰጡ ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በንቃት ስለመሳተፋቸው፤ /0.5%/	የተወሰኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ የሚሰጡ ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በንቃት ተሳትፈዋል፡፡	አብዛኛው ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ የሚሰጡ ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በንቃት ተሳትፈዋል፡፡	ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ የሚሰጡ ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በንቃት ተሳትፈዋል፡፡

15.4.	የተማሪዎች በክፍል ውስጥና ውጪ ጥያቄዎችን የመጠየቅና መልሶችን የመመለስ ተሳትፎ ስለማድረጋቸው፤ /1%/	ጥቂት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄዎችን የመጠየቅና መልሶችን የመመለስ ተሳትፎ አድርገዋል፤	አበዛኛዎቹ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄዎችን የመጠየቅና መልሶችን የመመለስ ተሳትፎ አድርገዋል፤	ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄዎችን የመጠየቅና መልሶችን የመመለስ ተሳትፎ አድርገዋል፤
15.5.	ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ ስለማድረጋቸው፣ /0.5%/	አበዛኛዎቹ ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ አያደርጉም፤	ጥቂት ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፤	አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተለያዩ ክበባት በመደራጀት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፤
